# የብሉይ ኪዳን መሠረታዊ ትምህርቶች

## የኦሪት መጻሕፍት ከጥንታዊዉ ታሪክ እና ከአባታችን አብርሃም ጋር

### የኮርስ መግለጫ

የብሉይ ኪዳን የመጀመሪያዎቹ አምስት መጻሕፍት በተለምዶ የኦሪት መጻሕፍት ይባላሉ። የእስራኤልን ሕዝብ ከፍጥረት ጀምሮ የተስፋይቱን ምድር ድል ለማድረግ እስካለው ዝግጅት ድረስ ያለውን ታሪክ ይነግሩናል። የኦሪት መጻሕፍት ግን በእግዚአብሔር ስለ ተመረጠው ሕዝብ ታሪካዊ ዘገባ ነው ወይስ ሌላ ከዚያ የሚያልፍ ነገር አለው? ይህ ኮርስ የዘፍጥረት እና የዘፀአት መጽሐፍትን በመመርመር ለምን እንደተፃፉ፣ ለቀደሙት ታዳሚዎቻቸው ምን ትርጉም እንዳላቸው እና ዛሬ ለእነዚህ መጽሐፍቶች ምን አይነት ምላሽ መስጠት እንዳለብን ይመረምራል። ይህ ኮርስ በ *አሪት መጻሕፍት* ፣ *ጥንታዊ ታሪክ* እና *በአባታችን አብርሃም*፣ ተከታታይ ትምህርቶች ላይ የተመሠረተ ሲሆን በሰርድ ሚሌኒየም ሚኒስትሪ ተዘጋጅቶ በዶክተር ስኮት ሬድ እና በዶክተር ሪቻርድ ኤል.ፕራት ጁኒየር አስተናጋጅነት ከተለያዩ ፕሮፌሰሮች በተሰጡ አስተዋጾ የቀረበ ነው።

### ግቦች እና አላማዎች

**ግቦች**

በዚህ ኮርስ፥ የሚከተሉትን ማከናወን እንፈልጋለን፡-

1. የኦሪት መጻሕፍት ለምን እንደተጻፉ፣ ለቀደሙት ታዳሚዎቻቸው ምን ትርጉም እንዳላቸው እና ዛሬ ለእነዚህ መጻሕፍቶች ምን አይነት ምላሽ መስጠት እንዳለብን ለማወቅ ሙሉ ትምህርቱን እንደምትጠቀሙ ተስፋ እናደርጋለን።

2. በእግዚአብሔር ጸጋ እና ፍቅር በተሞላበት ሉዓላዊ ምሪቱን ታምናችሁ በእምነታችሁ እንደምታድግገ ተስፋ እናደርጋለን።

3. ሳታወላዱ በእምነት እየኖራችሁ የኦሪት መጻሕፍትን ትምህርት በራሳችሁ ህይወት ላይ እንደምትተገብሩ ተስፋ እናደርጋለን።

**ዓላማዎች**

የሚከተለውን ስታደርጉ፥ ግቦቹን ማሟላታችሁን ያሳያል፡-

1. በፈተናህ አጥጋቢ ውጤቶችን በማግኘት የኦሪት መጻሕፍት አወቃቀር፣ ይዘት፣ ዋና ትርጉም እና በአሁኑ ዘመን የሚኖረውን አተገባበርን በተመለከተ ቁልፍ መረጃዎችን መለየት እንደምትችሉ ያሳያል።

2. ትምህርቱን በህይወታችሁ እንዴት እንደተገበራችሁት እና በተለይም ደግሞ እንዴት በእምነት እንደምትኖሩት፣ በእግዚአብሔር ፀጋ እና በእሱ ፍቅር በተሞላበት ሉዓላዊ ምሪት እየታመናችሁ መሆናችሁን እየሳያችሁ በጥናት መመሪያው ውስጥ ያሉትን የአተገባበር ጥያቄዎችን መልሱ።

### የትምህርቱ ዝርዝር ጭብጥ

1. የኦሪት መጻሕፍት መግቢያ
2. ፍጹም ዓለም

3. ጠፍቶ የተገኘ ገነት
4. የዓመፅ ዓለም
5. ትክክለኛው አቅጣጫ
6. የአብርሃም ሕይወት፡ መዋቅር፣ ይዘት እና የመጀመሪያው ትርጉም
7. የአብርሃም ሕይወት፡ በአሁኑ ዘመን ሲተገበር
8. አባታችን ያዕቆብ
9. ዮሴፍ እና ወንድሞቹ
10. የዘፀአት አጠቃላይ እይታ

**የቤት ስራ ማብራሪያዎች**

*የመልቲሚዲያ ትምህርቶች*

1. ቪዲዮውን በመመልከት፥ ኦዲዮውን በማዳመጥ ወይም፥ ጽሑፉን በማንበብ ***ትምሕርቱን*** አጥና።
2. ለእያንዳንዱ ትምህርት ***የጥናት መመሪያውን*** አጠናቅ። እነዚህ የጥናት መመሪያዎች ለኦንላይን ጥያቄዎች እንድትዘጋጅ እና ትምህርቱን በራስህ ህይወት ላይ ተግባራዊ እንድታደርግ ይረዱሀል።
3. ለእያንዳንዱ ትምህርት ኦንላየን ላይ ያሉትን ***አጭር ፈተናዎችን*** ውሰዱ። አጭር ፈተናዎቹን የፈለጋችሁትን ያህል ጊዜ መውሰድ ትችላላችሁ፣ነገር ግን በእያንዳንዱ ሙከራ መካከል የአንድ ሰአት ልዩነት መኖር አለበት። ከፍተኛው ነጥብህ ይፋዊ ነጥብህ ይሆናል። ፅንሰ-ሀሳቦቹን በትክክል መረዳትህን ለማረጋገጥ በሳምንታዊው ውይይት ላይ ከመሳተፋችሁ በፊት ቢያንስ 80% ማሳካት እንዳለባችሁ እንመክራለን።
4. ***የውይይት መመሪያውን*** በመጠቀም፥ ከቡድናችሁ እና ከአሰልጣኛችሁ ጋር አንድ ላይ በሳምንታዊው ***ውይይት*** ተካፈሉ። እነዚህ ውይይቶች የትምህርቱን ይዘት ሙሉ በሙሉ ለመረዳት እና ፅንሰ-ሀሳቦቹን በህይወታችሁ እና በአገልግሎታችሁ ላይ በትክክል ለመተግበር ለመቻላችሁ በጣም አስፈላጊ ናቸው። በቪዲዮ ትምህርቶች ላይ የሚደረጉት ውይይቶች ቢያንስ አንድ ሰዓት እንዲሞሉ እንመክራለን።
5. ***የብሉይ ኪዳን መሠረቶችን - የመጨረሻ ፈተና*** ውሰድ። ፈተናውን ደግመህ የፈለከውን ያህል ጊዜ መውሰድ ትችላለህ፣ ነገር ግን በእያንዳንዱ ሙከራ መካከል የአንድ ሰአት ልዩነት መኖር አለበት። ኦፊሴላዊው ውጤታችሁ ከፍተኛው ነጥብህ ሲሆን የሚቀጥለውን ኮርስ ከመቀጠላችሁ በፊት ቢያንስ 80% ማግኘት አለባችሁ።

*የደቀመዝሙርነት ባጅ*

1. በየሳምንቱ አንድ ሰዓት ***የደቀ መዝሙር ባጅ መመሪያዎችን*** አጥንቶ ለመጨረስ ጊዜ መወሰን አለበት። ይህንን አስፈላጊ የሆነ የአገልግሎት ክህሎት ለማዳበር በምታደርጉት ጥረት ይህ ከአንድ እስከ ሁለት ገጽ ያለው መመሪያ ለአሰልጣኞቻችሁ አጠቃላይ መመሪያ ይሰጣል።

2. በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ሳምንታት ውስጥ፣ በወንጌል ስርጭት ባጅ በተሰጠው መመሪያ በዚያ ሳምንት የሚኖራችሁን አንድ ሰዓት ውስጥ ***የውይይት ርዕሶች*** ለማየት ተጠቀሙ።
3. በቡድን የውይይት ጊዜያት አማካኝነት ጠንካራ መሰረት ከተጣለ በኋላ፥ ቀሪዎቹን ሳምንታት ***የተግባር እርምጃዎች*** ባጅ በማየት ላይ በመስራት አሳልፉ።
4. አሰልጣኙ ከባጅ መመሪያዎች አንጻር የተግባር እርምጃዎቹን መጠናቀቅ ከወሰነ በኋላ ባጁን ትሸለማለህ። ሁሉም ባጆች በኦንላየን ክፍል ውስጥ በሚገኙት በተማሪዎች "የጀርባ ቦርሳ" ላይ  ይታያሉ።

**ውጤት**

የመጨረሻው ውጤት እንደሚከተለው ይሰላል፦

1. በክፍሉ ውስጥ ከተደረገው ሌክቸር የተውጣጣ አጫጭር ፈተና እያንዳንዱ 30 ነጥብ ይያዛል።
2. ከሌክቸሩ የሚወጣው የመጨረሻው ፈተና 100 ነጥብ ይይዛል።
3. የደቀ መዛሙርትነት ባጅ ሪፖርት በውጤታችሁ ላይ ለውጥ አያመጣም ነገር ግን ኮርሱን ለማጠናቀቅ መግባት አለበት።

*ከ80% በላይ አጠቃላይ የኮርስ ውጤት እንደ ማለፍያ ነጥብ ይቆጠራል።*